በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ክፍል ፮

**መምህር፡-** ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ሚያዝያ ፪ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ

- *‹‹አትስረቅ።››* ***ዘጸ 20፡15፣ ዘዳግ 5፡19፡፡***
- «ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።» ***ቀዳ ቆሮ 6፡10፡፡***

## *ሌብነት ምንድር ነው? የምንሰርቀውስ ከማን ነው?*

- ሌብነት የአንዱን ሰው ንብረት መካፈል ማለት አይደለም፡፡ «በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በሰንበት ቀን በእርሻ መካከል አለፈ፤ ደቀ መዛሙርቱም ተራቡና እሸት ይቀጥፉ ይበሉም ጀመር። ፈሪሳውያንም አይተው። እነሆ፥ ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ አሉት።» ***ማቴ 12፡1-2፡፡*** እንዳለው ደቀ መዛሙርቱን ጌታችን ሲገስጻቸው አልተመለከትንም፡፡ ይህም የተራበ ሰው በጎዳናው ያገኘው እሸት ቢኖር ከዚያ ቀጥፎ ከረሐቡ እንዲታገስለት ማድርግ የተፈቀደ መሆኑን ያመለክታል፡፡
- «ወደ ባልንጀራህ ወይን ቦታ በገባህ ጊዜ እስክትጠግብ ድረስ ከወይኑ ብላ ወደ ዕቃህ ግን ከእርሱ ምንም አታግባ። ወደ ባልንጀራህ እርሻ በገባህ ጊዜ እሸቱን በእጅህ ቀጥፈህ ብላ ወዳልታጨደው ወደ ባልንጀራህ እህል ግን ማጭድ አታግባ።» ***ዘዳግ 23፡24-25፡፡***
- በባለቤቱ ፈቃድ ተካፍለን ወስደን እንደሆነ ይህ ሌብነት አይባልም፡፡
- የተወሰደበት ሰው ሳያውቅ - ይሁዳ ደቀ መዛሙርቱ ሳያውቁ ለራሱ እንደወሰደው ወይም ቤቶችን ሰብረው በመግባት ሌቦች እንደሚያደርጉት ያለ ድርጊት ሌብነት ይባላል፡፡ «ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው።» ***ዮሐ 12፡6***፣ «ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፡፡» ***ማቴ 6፡19፡፡***

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ

- ነገር ግን ፍጹም ከሆነ በባልንጀርነት የተነሳ ለባልንጀራችን የሆነውን ለራሳችን ብናደርገው እስከነገርነውና ፈቃዱም ሆነ ይቅርታው እስከተደረገልን ድረስ የምናደርገው ሌብነት አይባልም፡፡
- ሌላው የሌብነት ዓይነት ምስጢራዊ ሌብነት ነው፡፡ ይህም ማጭበርበርን ወይም ማታለልን፣ ሕገ ወጥ ሰነድ ማዘጋጀትም ሆነ መጠቀምን… ይመለከታል፡፡ በዚህ ድርጊት ውስጥ የውሸት ኃጢአት ይገኛል፡፡
- ሌብነት ወይም መስረቅ የተሰረቀው ሰው እያየና እየሰማ ያለፈቃዱ ሊፈጸም ይችላል፡፡ ይህም በኃይል ወይም ትጥቅ ታጥቆ ሊፈጸም ይችላል፡፡ ይህም ድርጊት በተጠቂው ላይ የአካል ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- መስረቅ ከማውደምም ጋር ሊያያዝ ይችላል፡፡ ሆን ብሎ የሌላውን ሰው ንብረት ማውደምና ንብረቱንም እንዲያጣው ማድረግ ከሌብነት ሊቆጠር ይችላል፡፡ ይህን ጉዳት ያስከተለ ሰውም ንብረቱን መጠገን ወይም መመለስ ይጠበቅበታል፡፡
- ጥላቻውን ለማርካት ብቻ ሆን ብሎ  የሌላውን ንብረት የሚያወድም ሰው ፍቅር የጎደለው ሰው ነው፡፡ እንዲህ ያለ ድርጊትም የሕዝብ ንብረት ማውደምን ይጨምራል፡፡ በጎዳና ግርግር የመንገድ መብራቶችን መሰባበር፣ ዛፎችን መገንደስ፣ የሕዝን አውቶቡሶችን ማቃጠል የአገርን ሀብትና የሕዝብን ንብረት መስረቅ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
- በአጠቃላይ ሌብነት ወይም ስርቆት ለሌሎች ሰዎች መብትና ንብረት ያለንን ንቀት የሚያሳይ ድርጊት ነው፡፡
- ሌብነት የሰራቂውን ሰው ክፋትና አለመታመን የሚያሳይ፣ በሰውም ዘንድ ያለውን ተቀባይነት የሚያሳጣ ሰውም እንዳይቀርበው የሚያደርግ ድርጊት ነው፡፡
- ይሁን እንጂ ይህ ጉዳይ የራሳቸውንና የሌላውን ሰው ቁሳቁስና ንብረት ለይተው ለመረዳት በማይቻላቸው ሊጋ ወጣቶች ቢከሰት ፈጽመን እንዳናገላቸው መጠንቀቅ ያስፈልገናል፡፡ በእውቀት፣ ሥነልቦናና ስሜት እየበሰሉ ሲሄዱ ራሳቸው ይስተካከላሉና፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ

- ሌብነት አንዳንድ ጊዜ ቅጣትን ሳይሆን ሥነ-ልቦናዊ ሕክምናን የሚፈልግ ሕመም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሕመም ያለበት ሰው እንዴት እንደሚጠቀምበት የማያውቀውን ማንኛውንም ያገኘውን ቁሳቁስ ወስዶ ሊያስቀምጥ ወይም ከሌሎች እይታ ሊሰውረው ይችላል፡፡ የሚያደርገውም ከቁጥጥሩ ውጪ በሆነ መንገድ ስለሆነ ባደረገውም ፈጽሞ ሊያለቅስ ይችላል፡፡ እንዲህ ያለው ሰው ችግር ከቀድሞ ታሪኩ፣ ከኖረበት ወይም ካደገበት አካባቢ ተጽእኖ፣ ከአስተዳደጉ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡
- እርስ በርስ በመተማመን በእርጋታ መኖር ምን ያህል የሚያስደስት ነው? ማንኛውንም ነገር በየትኛውም ሥፍራ አስቀምጠን ተመልሰን ማንም ሳይነካው ማግኘት፣ በራችንን ከፍተን ሄደን ተመልሰን ያለምንም ችግር መልሰን ማግኘት ምንኛ መልካም ነው!
- ላባም ያዕቆብን « ነገር ግን አምላኮቼን (ጣዖታቱን) ለምን ሰረቅህ?» ***<u>ዘፍጥ 31፡30፡፡</u>*** ብሎ በወነጀለው ጊዜ ያዕቆብ የጥፋቱን ክብደት ተረድቶ « አምላኮችህን የምታገኝበት ሰው ግን እርሱ ይሙት የአንተ የሆነውም በእኔ ዘንድ ይገኝ እንደ ሆነ በወንድሞቻችን ፊት ፈልግ፥ ለአንተም ውሰደው አለ። » ***<u>ያዕ 31፡32፡፡</u>*** ይህም የተከሰተው ቅዱሱ ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊት ነበር፡፡
- ይህን የሚመስለውም ቅጣት በዮሴፍና በወንድሞቹ ታሪክ ውስጥ ይገኛል፡፡ ወንድሞቹ ጽዋውን ሰርቃችኋል ተብለው በተከሰሱ ጊዜ « ጌታዬ እንደዚህ ያለውን ቃል ለምን ይናገራል? ባሪያዎችህ ይህን ነገር የሚያደርጉ አይደሉም። እነሆ፥ በዓይበታችን አፍ ያገኘነውን ብር ይዘን ከከነዓን አገር ወደ አንተ ተመልሰናል ከጌታህ ቤት ወርቅ ወይስ ብር እንዴት እንሰርቃለን? ከባሪያዎችህ ጽዋው የተገኘበት እርሱ ይሙት እኛም ደግሞ ለጌታችን ባሪያዎች እንሁን።» ***<u>ዘፍጥ 44፡7-9፡፡</u>*** ብለዋል፡፡
- የማይዋሽ ሌባ ማግኘት ከባድ ነው፡፡ ሌባ የሆነ ሁሉ የሠራውን ጥፋት ለመሸፈን ይዋሻል፡፡ ሌባ ከሰረቀ በኋላ ብቻ ሳይሆን የሚሰርቀውን ሰው ለማታለል ሲል ሳይሰርቅም በፊት ይዋሻል፡፡ ስለዚህ ስለመስረቃችን በምንናዘዝበት ጊዜ ስለመዋሸታችንም መናዘዛችንን አንርሳ፡፡

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ</u>

<u>**የምንሰርቀው ከማን ወይም ምን ነው?**</u>

## 1. <u>*ከድሆች*</u>

- ከድሆች፣ ወላጅ አልባ ከሆኑ ልጆች፣ ባልዋ ከሞተባት ሴት መስረቅ በሌባው ልብ ምንም መልካምነት እንደሌለ ስለሚያመለክት ታላቅ ኃጢአት ነው፡፡ ጌታችንም « እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ፥ ወዮላችሁ፤ ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ።» <u>***ማቴ 23፡14***</u፡ « የመበለቶችን ቤት የሚበሉ ጸሎታቸውንም በማስረዘም የሚያመካኙ እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ። » <u>***ማር 12፡40፡፡***</u> በማለት ጻፎችና ፈሪሳውያንን የወቀሰው ለዚሁ ነው፡፡ እንዲህ ያሉትን በፍቅር መርዳት ሲገባን ለዳቦ መቅመሻ ያገኙአትን መንጠቅ ጭካኔ ነው፡፡
- « ከአንተ ጋር ለተቀመጠው ለወገኔ ለድህው ገንዘብ ብታበድረው፥ እንደ ባለ አራጣ አትሁን፥ አራጣም አትጫንበት። የባልንጀራህን ልብስ ለመያዣ ብትወስድ ፀሐይ ሳትገባ መልስለት፤ ሥጋውን የሚከድንበት እርሱ ብቻ ነውና የሚተኛበትም ሌላ የለውምና ወደ እኔም ቢጮኽ መሐሪ ነኝና እሰማዋለሁ።» <u>***ዘጸ 22፡25-27፡፡***</u>
- « ወንድምህ ቢደኸይ እጁም በአንተ ዘንድ ቢደክም፥ አጽናው እንደ እንግዳና እንደ መጻተኛም ከአንተ ጋር ይኑር። ወንድምህ ከአንተ ጋር ይኖር ዘንድ ከእርሱ ምንም ወለድ ወይም ትርፍ አትውሰድ ነገር ግን አምላክህን ፍራ። ብርህን በወለድ አታበድረው መኖህንም በትርፍ አትስጠው።» <u>***ዘሌዋ 25፡35-37፡፡***</u>
- « ለወንድምህ በወለድ አታበድር የብር ወይም የእህል ወይም የማናቸውንም ነገር ሁሉ ወለድ አትውሰድ።» <u>***ዘዳግ 23፡19፡፡***</u>
- አራጣ አበዳሪ ከድሃው የሚወስደው የበዛ ገንዘብ የድሃውን መሠረታዊ ነገር እንደመንጠቅ ወይም እንደ መስረቅ ይቆጥራል፡፡
- ባለጠጋውን መስረቅ ኃጢአት ከሆነ እንግዲህ ድሃውንም መስረቅ የባሰ ኃጢአት ነው፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ

**የምንሰርቀው ከማን ወይም ምን ነው? ...**

***2. ከተራ ሰዎች መስረቅ ኃጢአት ከሆነ ቤተ ክርስቲያንን ወይም ካህናትን መስረቅስ እንዴት ይታያል?***

- ንዋየ ቅዱሳትን ወይም አብያተ ክርስቲያናትን መስረቅ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው፡፡ በመላው ዓለም የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ከያዙአቸው ቅርሶች ጋር ያለጠባቂ ክፍት ሆነው ሳይዘጉ የምናገኛቸው ለዚሁ ነው፡፡
- ወደ እግዚአብሔር ቤት የምንመጣው ለንስሐ ነው፡፡ ሻማ፣ መጻሕፍትን፣ ጫማ... የሚሰርቁ ምን ይባላሉ?
- ከቤተ ክርስቲያን አልባሳት፣ ገንዘብ፣ ... ለራሳቸው ወይም ለቤታቸው የሚሰርቁስ? ይህ የእግዚአብሔር፣ የድሆችና የተቀደሰ ገንዘብ ነው፡፡
- የቅዱሳንን አጽም፣ ታሪካዊ ቅርሶችን... የሚሰርቁስ? የላሊበላ መስቀል (ተመልሷል)፣ በርካታ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት፣ ጽላቶች/ታቦታት፣ ... ከገዳማት ከአብያተ ክርስቲያናት «ለእውቀት ባለን ጥማት...» ያደረግነው ነው በሚል ሰበብ ተሰርቀዋል፡፡
- ከሁሉ በላይ ደግሞ እግዚአብሔርን ራሱ የሚሰርቁትንስ ምን እንላቸዋለን? አሥራቱን፣ በኩራቱንና ቀዳምያቱን ከመስጠት ተከልክለው እግዚአብሔርን የሚሰርቁት አሉ፡፡ ይህም ጉዳይ « ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምር ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል፥ እርስዋንም አልጠበቃችሁም። ወደ እኔ ተመለሱ፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፦ እናንተ ግን፦ የምንመለሰው በምንድር ነው? ብላችኋል። ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም። የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። በአሥራትና በበኵራት ነው። እናንተ፥ ይህ ሕዝብ ሁሉ፥ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ። በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፥ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡» ***ሚል 3፡7-10፡፡***
- ይህ ገንዘብ የቤተ ክርስቲያንና የድሆች ገንዘብ ነው፡፡ ለባለቤቱ ባለመስጠታችንም የተነሳ ጌታችን « የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ፥ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ።» ***ሉቃ 16፡9፡፡*** በማለት ነግሮናል፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ

**የምንሰርቀው ከማን ወይም ምን ነው? …**

*3. ሌላው ከእግዚአብሔር ና ከቤተ ክርስቲያን የምንሰርቀው ጊዜን ነው፡፡ የሰረቅነውንም ለራሳችን እንጠቀምበታለን፡፡ ለምሳሌም*

1. **የጌታን ቀን (ሰንበት)፡-** እግዚአብሔር በሳምንት ለእርሱ የምናደርጋት ዕለት (ሰንበት) አለችው፡፡ በዚያች ዕለት ለራሳችን እንደፈለግን እንድናደርግ አይገባንም፤ ዕለቲቱ ለእግዚአብሔርና ለአምልኮቱ ናትና፡፡ ለራሳችን የሥጋ ጉዳይ ካዋልን ግን የእግዚአብሔርን ቀን ሰርቀነዋል ማለት ነው፡፡
2. **የአምልኮ ጊዜያት፡-** በየዕለቱ ለጸሎት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ፣ ለቅዳሴ (ለኪዳን) … መንፈሳዊ ጉባኤያትን ለመሳተፍ ለእግዚአብሔር የሆነ ጊዜ አለ፡፡ እነዚህን ለማድረግ ዕድደ የማንሰጥ ከሆንን ከእግዚአብሔር እየሰረቅን ነው ማለት ነው፡፡ « አምላኬ፥ አምላኬ፥ ወደ አንተ እገሠግሣለሁ ነፍሴ አንተን ተጠማች፥ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች እንጨትና ውኃ በሌለበት በምድረ በዳ።» **መዝ 62(63)፡1**፣ « እኔ የሚወድዱኝን እወድዳለሁ፥ ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል።» **ምሳ 8፡17**፡፡ ያለን ለዚሁ ነው፡፡ እያንዳንዱን ዕለት ያለእግዚአብሔር የምንጀምር ከሆንን እግዚአብሔርን እየሰረቅን ነው ማለት ነው፡፡
3. **የእግዚአብሔር በዓላት፡-** እግዚአብሔር ለርሱ ብቻ የምናደርጋቸው የበዓላት ዕለታት አሉት፡፡ ለምሳሌ ሰሙነ ሕማማት፣ ትንሳኤ፣ ልደት፣ ስቅለት … ለእግዚአብሔር ካላደረግናቸው ሰርቀነዋል ማለት ነው፡፡

- ባሎች/ሚስቶች የወር ገቢያቸውን ባይገልጹ ወይም ቀንሰው ባያሳውቁ ሌብነት ነው፡፡ ማንኛውም ለባል የሆነ የሚስት እንደሆነ በግልጽ ተጋቢዎች የሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ መረዳት ይገባቸዋል፡፡
- የመሥሪያ ቤታችንን ቁሳቁስ፣ መኪና፣ አለቆች ከሆንን የበታች ሠራተኞቻችንን ጉልበት ሳይቀር ለግላችን ወይም ለራሳችን መጠቀም ቀላል ቢመስልም ስርቆት ነው፡፡
- የተዋስነውን ነገር ሳይፈቀድልን አረሳስተን ማስቀረትም ሌብነት ነው፡፡ ብዙዎች በዚህ መንገድ እስክሪብቶ፣ መጻሕፍቶቻቸውን አጥተዋል፡፡ ስለዚህ ስንዋስ ከማን እንደተዋስነው የሚገልጽ ማስታወሻ ከእቃው ጋር አብረን ብናስቀምጥ ለመመለስ ይረዳናል፡፡

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ</u>

## <u>የምንሰርቀው ከማን ወይም ምን ነው? …</u>

### *<u>4. በንግድ ዘርፍ የሚፈጸም ስርቆት</u>*

1. <u>በማታለል መስረቅ፡-</u> የተበላሸ ዕቃን ገዢው አለማስተዋሉን ምክንያት አድርገን መሸጥ፡፡ ገዢው ትኩረቱን ወደ ብልሽቱ እንዲያደርግ ማድረግ ብንችል ምንኛ ውብ ነው፡፡ በአትልክትና ፍራፍሬ መካከል የተበላሸውን፣ በከሰሉ ሥር የደቀቀውን፣… መሸጥ ስርቆት ነው፡፡ የንግድ ምልክቶችን በመውሰድ አስመስሎ ሠርቶ/አምርቶ (ብረቱን ወርቅማ ቀለም ቀብቶ አስመስሎ) ጥራቱን ያልጠበቀ ነገር መሸጥ ራሱ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የሸማቾችን ገንዘብ መንጠቅ ቄወም መስረቅ ነው፡፡ እንዲህ ባለ ሥራ የተጠመዱትም በሐሰት ፕሮፖጋንዳቸው የበዛ የማታለል ሥራ መሥራታቸው ኃጢአቱን የከፋ ያደርገዋል፡፡ የመለኪያ ሚዛኖችን ተጠቅሞም ማታለል ከዚሁ ይመደባል፡፡ ተጠቃሚውም በዚህ ድርጊት የተነሳ መጠንን በማሳነስ ማታለል ይፈጸምበታል፡፡
2. <u>በስግብግብነትና ዋጋን በመጨመር መስረቅ፡-</u> እግዚአብሔር ተገቢ የሆነ ትርፍ ከማግኘት በቀር ከራስ ወዳድነት የተነሳ ትርፍ እንድናግበሰብስ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን አልፈቀደልንም፡፡ ይህም ያልተፈቀደ ድርጊት በሞኖፖል (ምርትን) ለብቻ በመያዝ ገዢውን በማስጨነቅ ይፈጸማል፡፡ ምርቱን ሁሉ ከገበያ አሟጦ በመግዛት ከገበያ በማጥፋት በራስ ተመን ገዢውን ማስጨነቅ፡፡
3. <u>ኢኮኖሚያዊ ስርቆት፡-</u> ዋጋን ከፍና ዝቅ በማድረግ ዝቅተኛ አቅም ያላቸውን ነጋዴዎች ከገበያ በማውጣት የሚፈጸም ስርቆትም ከዚሁ ይመደባል፡፡
4. <u>በሸማቾች የሚፈጸም ስርቆት፡-</u> ሸማቾች በሚያደርጉት ክርክር ሻጩ የማስረዳት አቅም ከማጣት የተነሳ ወይም ሌሎች ክፍተቶችን በመጠቀም ራሳቸውንና ቤተ ሰቦቻቸውን ለመመገብ የማይበቃ ትርፍ እያተረፉ እንዲሸጡ ማታለል ስርቆት ነው፡፡

### *<u>5 ኢፍትሐዊነትና የሠራተኞችን ደመወዝ አለመክፈል</u>*

1. ለሠራተኞች ተመጣጣኝ የሆነ ደመወዝ አለመክፈል መስረቅ ብቻ ሳይሆን መግደልም ነው፡፡ « እግዚአብሔርም አለ፦ በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታቸውን ሰማሁ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ፡፡» *<u>ዘጸ 3፡7</u>*፡ « እነሆ፥ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል፥ የአጫጆችም ድምፅ ወደ ጌታ ፀባዖት ጆሮ ገብቶአል፡፡» *<u>ያዕ 5፡4፡፡</u>* እንዳሉ፡፡

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ</u>

<u>**የምንሰርቀው ከማን ወይም ምን ነው? ...**</u>

5. <u>*ኢፍትሐዊነትና የሠራተኞችን ደመወዝ አለመክፈል…*</u>

2. ደመወዝ ማዘግየትን ወይም ዕድገትን መከልከልን ስርቆት መሆኑን አስመልክቶም «ድሀና ችግረኛ የሆነውን ምንደኛ፥ ከወንድሞችህ ወይም በምድርህ በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚቀመጡት መጻተኞች ቢሆን፥ አታስጨንቀው። ድሀ ነውና፥ ነፍሱም ጠንክራ ትፈልገዋለችና ወደ እግዚአብሔር እንዳይጮኽብህ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ደመወዙን ፀሐይ ሳይገባ በቀኑ ስጠው።» <u>*ዘዳግ 24፡14-15፡፡*</u> ብሎናል፡፡ ይህም መክፍል ከሚገባቸው በላይ ወይም በታች የሚገምቱ የግብር ሰብሳቢ አካል ሠራተኞችንም ይመለከታል፡፡ ሉቃ 19፡8፡፡

3. ጉቦ፡- ለሠራው ሥራ ደመወዙን የሚቀበል ሠራተኛ አገልግሎት ከሰጠው ወገን ሌላ ምንም መጠበቅ የለበትም፡፡ ጉቦ የሚቀበል ከሆነ ግን ስርቆት ነው፡፡ ጉቦን መቀበልም በመንግሥት የተጫነበትን ግብር ለማስቀነስ፣ ጉዳዩን ከተገቢው ጊዜ በላይ ለማፋጠን … ሲባል ነው፡፡ አገልግሎት ካገኘንበት ምግብ ቤት የሚገኙ ገቢያቸው አነስተኛ ለሆኑ ሠራተኞች የምንሰጠው ቲፕ ግን ጉቦ አይባልም፡፡

4. በሥራ ገበታ ላይ አለመታመን፡- ተገቢ ያልሆነ ፈቃድ በመውሰድ ወይም የሥራ ሰዓት ባለማክበር፣ ታምኖ በተገቢው ፍጥነትና ብቃት ሥራን አለመሥራት፣ ለሥራ የምንገለገልባቸውን ቁሳቁሶች ያላግባብ ማውደም ስርቆት ነው፡፡ ለዚህ ጉዳይ የራሳቸውን ታክሲ የሚያሽከረክሩና ተቀጥረው የሚያሽከረክሩ ሾፌሮች ጥሩ ማሳያ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

5. ሥልጣንን በመጠቀም ሕገ ወጥ ስምምነቶችን (ኮንትራት ውሎችን መፈጸም) ማድረግ ወይም የሌላውን ንብረት መውሰድ <u>*ቀዳ ነገ 20፡1-ፍም*</u>፡ ሕግን ለራስ አመቺ በሆነ መንገድ እያጣመሙ በመተርጎምም ራስን ተጠቃሚ ማድረግ ስርቆት ነው፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ

**<u>የምንሰርቀው ከማን ወይም ምን ነው? …</u>**

## *6. <u>ስምምነትን ወይም ውልን በማፍረስ መስረቅ</u>*

1. ውልን ማፍረስ «ማናቸውም ሰው ኃጢአትን ቢሠራ፥ እግዚአብሔርንም ቢበድል፥ ያኖረበትን አደራ ወይም ብድር ወስዶ ባልንጀራውን ቢክድ፥ ወይም ቢቀማ፥ ወይም በባልንጀራው ላይ ግፍ ቢያደርግ ወይም የጠፋውን ነገር ቢያገኝ፥ ያንንም ሸሽጎ በሐሰት ቢምል፥ ሰው ከሚያደርጋቸው ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ በአንዲቱ ቢበድል፥ እርሱ ኃጢአትን ሠርቶ በደለኛ ቢሆን፥ በቅሚያ የወሰደውን ወይም በግፍ የተቀበለውን ወይም የተሰጠውን አደራ ወይም ጠፍቶ ያገኘውን፥ ወይም በሐሰት የማለበትን ነገር ይመልስ በሙሉ ይመልስ፥ ከዚያም በላይ አምስተኛውን ክፍል ጨምሮ የበደሉን መሥዋዕት በሚያቀርብበት ቀን ለባለ ገንዘቡ ይስጠው። ስለ በደል መሥዋዕትም ለእግዚአብሔር ከመንጋው ነውር የሌለበትን አውራ በግ እንደ ግምጋሜህ መጠን ስለ በደል መሥዋዕት ወደ ካህኑ ያምጣ።ካህኑም በእግዚአብሔር ፊት ያስተሰርይለታል፥ ስለዚያም ስላደረገው በደል ሁሉ ይቅር ይባላል። » ***<u>ዘሌዋ 6፡2-7፡፡</u>*** በማለት ንስሐ የሚያሻው ኃጢአት መሆኑን ይነግረናል፡፡
2. በገንዘብ ልውውጥ ጊዜ በስህተት አልፎ የተሰጠንን ገንዘብ በሙሉ አለመመለስም ስርቆት ነው፡፡
3. በቁማር ከሌላው ሰው የተወሰደ ገንዘብም ያለፍትሕ የተወሰደ ስለሆነ ስርቆት ነው፡፡ ሕጻናትን አታሎ ገንዘባቸውን መውሰድም እንዲሁ ስርቆት ነው፡፡
4. በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በሌብነት ድርጊት ተባባሪ መሆን ራሱ ሌብነት ሆኖ ይቆጠራል፡፡ « ከሌባ ጋር የሚካፈል ነፍሱን ይጠላል መርገምን ይሰማል፡፡» ***<u>ምሳ 29፡24፡፡</u>***

# አሠርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ

**የምንሰርቀው ከማን ወይም ምን ነው? …**

## 7. *የሰውን በጎ ሐሳብ ወይም ምስጢር መስረቅ*

1. የአንድን ሰው ጽሑፍ፣ ግጥም፣ ዜማ፣ እቅድ ወይም በአጠቃላይ ሥራ ወስዶ የራስ አስመስሎ ማቅረብ ስርቆት ነው፡፡
2. በፈተና ወቅት መስረቅ፣ የአንድ ሰው ፈጠራ፣ የትምህርት መረጃ፣ ሐሳቡን መስረቅ ወይም በማንኛውም የሥልጣን እርከን ለጉዳዩ ተባባሪ መሆን ስርቆት ነው፡፡
3. ምስጢርን መስረቅ፡- የሰውን ደብዳቤ ማንበብ (የልጆቻችንንም ቢሆን አሳምነን ወይም በንስሐ አባቶቻችን ፈቃድ እንዲያምኑበት አድርገን ከላሆነ በቀር)፣ መስማት የሌለብንን መስማት፣ … ሌብነት ነው፡፡

## 8. *ሌሎች የስርቆት ዓይነቶች*

- አገርን በቅኝ ገዢነት ወይም በኃይል በመውረር ፣ ነፍሳትን በክህደት ትምህርት ወይም እንግዳ ትምህርትን በሚከተሉ አማካይነት መስረቅ ሌብነት ነው፡፡ **<u>ዮሐ 10፡8፡፡</u>** ታላቁ የሕግ መምህር ገማልያል « ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳስ። እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ ተነሥቶ ነበርና፥ አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበተኑ እንደ ምናምንም ሆኑ። ከዚህ በኋላ ሰዎች በተጻፉበት ዘመን የገሊላው ይሁዳ ተነሣ ብዙ ሰዎችንም አሸፍቶ አስከተለ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበታተኑ። አሁንም እላችኋለሁ። ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ ተዉአቸውም፤ ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደ ሆነ ይጠፋልና፤ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም፥ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ።» **<u>የሐዋ 5፡36-39፡፡</u>** በማለት ስለዚሁ ሰራቂዎችንና እውነተኞቹን በማንሳት አውስቷል፡፡
- እነዚህም የአርዮስ፣ የመቅዶንዮስ፣ የንስጥሮስ… ተከታዮች ሆነው የበተ ክርስቲያንን ልጆች የሚነጥቁ ናቸው፡፡ ቅዱስ መጽሐፍም እነዚህኑ አስመልክቶ « ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት፤ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና።» ***<u>ካል ዮሐ 10-11፡፡</u>*** በማለት ያስጠነቅቀናል፡፡

# አሥርቱ ትእዛዛት - ሰባተኛው ትእዛዝ

## ለስርቆት የሚያነሳሱ ምክንያቶች

- ክፉ ምኞት፣ ገንዘብን መውደድ፣ ለሌሎች ፍቅር ማጣት፣ የሌሎችን መብት አለማክበር፣ ጭካኔ፣ ምሕረት የለሽ መሆን.. ሊጠቀሱ የሚችሉ ለስርቆት የሚያነሳሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡
- ከቤተሰብ ሌብነትን መውረስ፣ አስመሳይነት ወይም የተበላሸ አስተዳደግና፣ ድህነትም ለሌብነት መነሻ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- ሌብነት ለደከመች ነፍስ በሽታ፣ ልምድ ወይም ደስታ ሊሆን ይችላል፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን « የስርቆት ውኃ ይጣፍጣል፥ የተሸሸገም እንጀራ ደስ ያሰኛል።» ***ምሳ 9፡17፡፡*** በማለት እንደጻፈልን፡፡
- ሌብነት በባለጠጎች ሲፈጸም ስግግብነት ወይም በሽታና ገንዘብን መውደድ ነው፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን « ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ፥ ባሕሩ ግን አይሞላም ፈሳሾች ወደሚሄዱበት ስፍራ እንደ ገና ወደዚያ ይመለሳሉ።» ***መክ 1፡7፡፡*** በማለት እንደጻፈልን፡፡
- በድሆች የተፈጸመ ስርቆትም ጉድለታቸውን ለመሙላት ያደረጉት ስለሆነ ፍትሐዊ ሆኖ አይቆጠርም፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን « ሌባ በተራበ ጊዜ ነፍሱን ሊያጠግብ ቢሰርቅ ሰዎች አይንቁትም ቢያዝም ሰባት እጥፍ ይከፍላል፥ በቤቱም ያለውን ሁሉ ይሰጣል።» ***ምሳ 6፡30-31፡፡*** በማለት እንደጻፈልን፡፡

## መፍትሔዎች

- የመጀመሪያው መፍትሔ የታማኝነትን፣ ሌሎችን የምንወድበትን ጽኑ ፍቅርና መብታቸውን የምናከብርበትን ይዘን ሕይወት ይዘን ከልጅነት ዘምሮ አብሮ ማደግ ነው፡፡ እንደዚህ ካደግን ጠፍቶ ተተገኘነውን ለባለቤቱ የመመለስ፣ እርስ በርስም የመከባከብ ሕይወት ይኖረናል፡፡
- ሌላች መፍትሔዎች ጠንክሮ መሥራት፣ ያለኝ ይበቃኛል ማለት፣ ቅንጦትን አለመውደድ፣ እንደ አቅም መኖር፣ በየጭፈራ ቤቱ አለመገኘት፣ ከትዳር ውጪ ግኙኝነትን አለመመሥረት፣ ቅማርተኝነትን ከራስ ማራቅ፣ ወዘተ ናቸው፡፡

## ለስርቆት የሚያስፈልግ ንስሐ

- መናዘዝና የወሰዱትን መመለስ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ « እርሱ ኃጢአትን ሠርቶ በደለኛ ቢሆን፥ በቅሚያ የወሰደውን ወይም በግፍ የተቀበለውን ወይም የተሰጠውን አደራ ወይም ጠፍቶ ያገኘውን፥ ወይም በሐሰት የማለበትን ነገር ይመልስ በሙሉ ይመልስ፥ ከዚያም በላይ አምስተኛውን ክፍል ጨምሮ የበደሉን መሥዋዕት በሚያቀርብበት ቀን ለባለ ገንዘቡ ይስጠው።…» ***ዘሌዋ 6፡4-5፡፡*** « ሰው በሬ ወይም በግ ቢሰርቅ፥ ቢያርደው ወይም ቢሸጠው፥ በበሬው ፋንታ አምስት በሬዎች፥ በበጉም ፋንታ አራት በጎች ይክፈል።» ***ዘጸ 22፡1፣ ዘጸ 227-8፣ ምሳ 6፡30-31፡፡***
- ዘኬዎስ « ጌታ ሆይ፥ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደ ሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ አለው።» ***ሉቃ 19፡8፡፡*** እንደተናገረው ሌባ የሰረቀውን እጥፍ አድርጎ ቢያንስ የሰረቀውን መመለስ ይኖርበታል፡፡ ይህን ሲያደርግ ማንነቱ እንዲገለጥ ካልፈለገ ደግሞ መመለስ የሚያስችለውን ሌላ ጤናማ መንገድ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት - ስምንተኛው ትእዛዝ

*‹‹በሐሰት አትመስክር›› ዘጸ 20፡16፡፡*

- « በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።» ዘጸ 20፥16፤ ዘዳግ 5፡20፡፡
- « ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው እውነትን የሚያደርጉ ግን በእርሱ ዘንድ የተወደዱ ናቸው።» ምሳ 12፡22፡፡
- « አትስረቁ፥ አትካዱም፥ ከእናንተም እርስ በርሳችሁ ሐሰት አትነጋገሩ።» ዘሌዋ 19፡11፡፡
- « ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ።» ኤፌ 4፡25፡፡

*የሐሰት ዓይነቶች*

- ሐሰተኛ ምስክር መሆን ሐሰተኛነት ሲሆን ከፍ ያለ ክፋት ነው፡፡ ፈሪነታችንንና ደካማነታችንንም የሚያመላክት ነው፡፡ በአንጻሩ እውነተኛ ሰው ለድርጊቱ ኃላፊነትን መውሰድ የሚችልበት ትከሻ ያለው ብርቱ ነው፡፡
- ሐሰት በማያስተውል ደካማ ሰው ሕይወት የሚገኝ መፍትሔ ነው፡፡ ይህም ሰው ከአንድ ወደ ሌላው እየቀጠላ የማያቋርጥ ውሸት ይዋሻል፡፡
- የሐሰተኛ ሰው እውነትም ቢናገር የሚያምነው ማንም የለም፡፡ ሐሰት የብዙ ኃጢአቶች ጥርቅም ነው፡፡ ስለዚህ የንስሐ አባቶች ስለሐሰተኛነቱ የሚናዘዘውን ሰው ምን እንዳነሳሳው መጠየቅ ይገባቸዋል፡፡
- የመጀመሪያው ሐሰተኛ ዲያቢሎስ ነው፡፡ «ሞትን አትሞቱም፡፡» ዘፍጥ 3፡4፡፡ በማለት አዳምንና ሔዋንን ዋሽቶአቸዋል፡፡ የዋሸበትም ምክንያት ህሕይወታቸው መቅናቱና ሊያጠፋቸው መፈለጉ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም « እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።» ዮሐ 8፡44 በማለት ስለ ዲያቢሎስ ነግሮናል፡፡

<u>*ሐሰት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊፈጸም ይችላል*</u>

- ሐሰትን የሚናገር እርሱ ሐሰተኛ ነው፡፡ ሐሰተኛ ወሬዎችን የሚያወሩም እንዲሁ ሐሰተኛ ናቸው፡፡
- አንዳንድ ጠባብ አእምሮ ያላቸው ሰዎች የሰሙትን ሁሉ ሳይመዝኑና ሳይፈትኑ በማመን እንደእውነት ይነዙታል ወይም ያዳርሱታል፡፡

# አሥርቱ ትእዛዛት - ስምንተኛው ትእዛዝ

***ሐሰት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊፈጸም ይችላል***

- እንዲህ ያሉትን ጥበብ የጎደላቸው ናቸው እንላቸዋለን፡፡ «እንደ እባብ ብልሆች እንደ ርግብም የዋህ ሁኑ፡፡» ***ማቴ 10፡16፡፡*** ይህም ማለት ጉዳት የሌላችሁ ቀናና ጥበበኛ ሁኑ ማለት ነው፡፡
- ስለዚህ ሕዝቡን ሁሉ የምንመክረው «የተባለውን ነገር ሁሉ አትመኑ፡፡» ወይም «ሳትመረምሩ አትፍረዱ፡፡» ብለን ነው፡፡
- በምንኖርበት ዓለም ሐሰት ስላለ ከማመናችን በፊት መመርመርና መፈተሽ የእኛ ኃላፊነት ነው፡፡ ለዚህ ነው ቅዱስ መጽሐፍ በአዲስም በብሉይም በመደጋገም የምስክሮችን አስፈላጊነት የነገረን፡፡ « በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች አፍ ሞት የሚገባው ይገደል በአንድ ምስክር አፍ አይገደል።» ***ዘዳግ 17፡6***፣ « ወደ እናንተ ስመጣ ይህ ሦስተኛዬ ነው፤ ሁሉ ነገር በሁለትና በሦስት ምስክር አፍ ይጸናል።» ***ካል ቆሮ 13፡1***፣ « ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፡፡» ***ማቴ 18፡16፡፡***
- የተነገረውንም ነገር ያመጣ ሰው ምስክር ሆኖ አይቆጠርም፡፡ ምክንያቱም ነገሩን ተሳስቶ የሰማ ሊሆን ይችላል፣ ኢጋኖ አቅርቦት ሊሆን፣ ከማይታመኑ ምንጮች ሰምቶት፣ ሆን ብሎ ሰውን ወይም ብዙዎችን ለመጉዳት ያወራ ወይም ያደረገ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡ «በድፍረትና በትዕቢት በመናቅም በጻድቅ ላይ የሚናገሩ የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ።» ***መዝ 30(31)፡18፡፡***
- ሰው ከመሬት ተነስቶ ወይም ከጠላት ከሰማው ወሬ የተነሳ በአግባብ ጉዳዩን ሳይመረምር የባልንጀራውን ማንነት መጠርጠሩ ኃጢአት ነው፡፡ ምንጮቹ ብዙ፣ ለረጅም ጊዜም የተነገሩ ቢሆኑ መመርመሩ ተገቢ ነው፡፡ ብዙዎች የተናገሩት ራሱ የተሳሳተ ምንጭ ይዘው የተነገረ ሊሆን ይችላልና፡፡ ብዙዎችም ተስማምተውና ፈጥረው ድምር ሐሰት ሊናገሩ ይችላሉ፡፡ የዮሴፍ ወንድሞችም ለአባታቸው ስለዮሴፍ « የልጄ ቀሚስ ነው ክፉ አውሬ በልቶታል ዮሴፍ በእርግጥ ተበጫጭቋል አለ።» ተብሎ እስክናነበው ድረስ ያደረጉት ይህንኑ ነበር፡፡ ***ዘፍጥ 37፡33፡፡***
- ስለዚህ ነገራቸው ጽድቅና እውነት እስካልሆነ ድረስ በብዙዎች ምስክሮችም ነገር መርካት የለብንም፡፡ ምክንያቱም እንደ ሊቀ ካህናቱ ብዙዎች በሐሰት በቅዱሳኑ ላይ መስክረዋልና፡፡ «የካህናት አለቆችና ሽማግሎች ሸንጎውም ሁሉ እንዲገድሉት በኢየሱስ ላይ የሐሰት ምስክር ይፈልጉ ነበር፡፡» ***ማቴ 26፡59፡፡***

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ስምንተኛው ትእዛዝ</u>

<u>**በቅዱሳን ላይ በሐሰት የመሰከሩ ምስክሮች**</u>

- ብዙ ሐሰተኞች በቅዱስ እስጢፋኖስ ላይ በተቃውሞ በሐሰት መስክረውበታል፣ አይሁድም ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር፡፡ « ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም፡፡» <u>*የሐዋ 6፡13፡፡*</u>
- ንግሥት ኤልዛቤል በናቡቴ ላይ በሐሰት ይመሰክሩ ዘንድ የሐሰት ምስክሮችን አምጥታ ነበር፡፡ « ሁለቱም ምናምንቴ ሰዎች ገብተው በፊቱ ተቀመጡ ምናምንቴዎቹ ሰዎችም በሕዝቡ ፊት። ናቡቴ እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቦአል ብለው በናቡቴ ላይ መሰከሩ። የዚያን ጊዜም ከከተማ አውጥተው እስኪሞት ድረስ ወገሩት። » <u>*ቀዳ ነገ 20፡13፡፡*</u>
- ቅዱስ ጳውሎስ ሁለት ሽማግሎችን ብዙ ሰዎች በሐሰት አገልግሎቱ እስኪታወክ ድረስ እንደከሰሱትም ነግሮናል፡፡ « በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ ራሳችንን እናማጥናለን፤ አሳቾች ስንባል እውነተኞች ነን፡፡» <u>*ካል ቆሮ 6፡8፡፡*</u> ክሱም በሐሰት ወሬ ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡
- በሐሰት የተከሰሱትን ቅዱሳን ነገር ሁሉ እንዳንዘረዝር ጊዜ ይገድበናል፡፡
- ቅዱስ አትናቴዎስ በዝሙትና በመግደል፣ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ታላቁ ቅዱስ መቃርስ ቅድስት እንባ መሪና በዝሙት፣ ደራጎንን የገደለው ቅዱስ ጊዮርጊስ መርዙን ጠጥቶ ምንም እንዳልሆነ ባዩት ጊዜ ጠንቋይ ተብለው በሐሰት ተከሰው ነበር፡፡
- ስለዚህ  በሐሰት ለሚከሱ ከሳሾች ጆሮን መስጠት ትክክል አይደለም፡፡
- «በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር» የሚለው ሕግም ሰሚዎችንም ተናጋሪዎችንም የሚመለከት ነው፡፡ ሐሰተኛን የሚሰማና የሚቀበለውም በውሸቱ እንዲቀጥል የሚያበረታታው ከመሆኑም በላይ ክፉ አድራጊዎችም እንዲከቡት ይፈቅዳል፡፡ « መኰንን ሐሰተኛ ነገርን ቢያደምጥ፥ ከእርሱ በታች ያሉት ሁሉ ዓመፅኞች ይሆናሉ።» <u>*ምሳ 29፡12፡፡*</u>
- በቤተ ክርስቲያናችንም ቀኖና ካህን ሐሰተኞችን የማይሰማ እንዲሆን መመዘኛ ተሰርቶለታል፡፡
- አንዳንድ ጊዜ ሐሰተኛ  ሊወጣው የማይችለው ችግር ውስጥ እስኪገባ ድረስ ቅዱሱን ሰው ይከሰው ዘንድ ይነሳል፡፡ ይህን የመሰለው ለዲያቢሎስ እንደ ጥበብ የሚቆጠር ነው፡፡

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ስምንተኛው ትእዛዝ</u>

<u>በቅዱሳን ላይ በሐሰት የመሰከሩ ምስክሮች</u>

- ቃላትን ወስደው የራሳቸው ጨምረው ወይም ካለው ቀንሰው ከትክለኛ ምንጭ እንደሰሙ አድርገው የሚያቀርቡ አሉ፡፡ የአባይ ውሃ ከሰማይ ሲዘንብ ቀለም አልባ ቢሆንም ሱዳን ወይም ግብጽ ሲደርስ ግን የተቀላቀለበትን አፈር ቀለም እንደሚይዝ የነገሩን እውነተኛ ገጽታ አጥፍቶ ቀባብቶ ማቅረብ ሐሰተኝነት ነው፡፡ ዓላማውም የሰውን ግኑኝነት ማበላሸት ነው፡፡
- በርካታ ዜናዎች በትክክል ከተፈጸሙት ድርጊቶች የተለየ ገጽታ ይዘው የምንሰማቸው ናቸው፡፡
- በዚህ ሂደት ራሳቸውን የማይከላከሉ ታማኞችና ዝምተኞች ጉዳት ያገኛቸዋል፡፡ ንጹሕ የሆነ ዮሴፍ የገጠመው ይኸው ነበር፡፡ ዘፍጥ 39፡1-ፍም፡፡
- «ኀጥኡን የሚያጸድቅና በጻድቁ ላይ የሚፈርድ፥ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊዎች ናቸው።» ***<u>ምሳ 19፡15፡፡</u>***
- ሐሰተኛውን የሚያጸድቅ ሐሰተኛ ምስክር ይባላል፡፡ ችሎታ እንደሌለው እያወቅን ድሃ ነው እረዳዋለሁ በሚል ምክንያት ብቻ የባልንጀራችንን ሥራ እንዲበድል ለሌለው ችሎታ ምስክርነት መስጠት በሐሰት መመስከር ነው፡፡
- በማዕረጋቸው ታላቅነት በሐሰት የሚመሰክሩ እጅግ በደል ያደርጋሉ፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች ደፍረው ያደረጉት ይህንኑ ነው፡፡ በንስሐ አባቱ ፊት ሐሰትን የሚናገርም እንዲሁ ነው፡፡ ሐናንያና ሰጲራም በእግዚአብሔር ፊት በሐሰት እስከመመስከር ደፍረው ነበር፡፡ ***<u>የሐዋ 5፡3-4፡፡</u>***
- ለእግዚአብሔር ለመዋሸት በመድፈር ከሚታወቁት ተጠቃሾቹ ሐሰተኛ ነቢያት፣ ሐሰተኛ ክርስቶሶች ሲሆኑ እግዚአብሔር ያልነገራቸውን በመናገር ይታወቃሉ፡፡
- «እኔም ሳልናገር። እግዚአብሔር እንዲህ ብሎአል ስትሉ፥ ከንቱ ራእይን ያያችሁ ውሸተኛንም ምዋርት የተናገራችሁ አይደላችሁምን?» ***<u>ሕዝ 13፡7</u>***፣ « አለምሁ አለምሁ እያሉ በስሜ ሐሰትን የሚናገሩትን የነቢያትን ነገር ሰምቻለሁ።» ***<u>ኤር 23፡25</u>***፣ « ሐዋርያት ነን የሚሉቱን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ፡፡ ***<u>ራእ 2፡2</u>***፣ « በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው።» ***<u>ካል ተሰ 2፡9</u>***፣ « ተራፊም ከንቱነትን ተናግረዋልና፥ ምዋርተኞችም ውሸትን አይተዋልና ሕልምንም የሚያዩ በሐሰት ተናግረዋል፥ በከንቱም ያጽናናሉ እረኛም የላቸውምና እንደ በጎች ተቅበዝብዘዋል ተጨንቀውማል።» ***<u>ዘካ 10፡2፡፡</u>***

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት - ስምንተኛው ትእዛዝ</u>

**<u>ሐሰት፡- ምክንያቱና መፍትሔው</u>**

- ሐሰት የሚያድነን መስሎን ወይም ጫና በዝቶብን መዋሸት ውጤቱ ታላቅ ገደልን በትንሽ እንጨት ለመሻገር መሞከር ነው፡፡
- ከመዋሸት ይልቅ ዝምታ የተሻለ አማራጭ ነው፡፡ ዝም እንበል፣ በተቻለን መጠን የንግሩን አቅጣች እንለውጥ፣ መልስ ባለመስጠታችን ይቅርታ እንጠይቅ፣ በተቻለን መጠን ሁሉ እውነቱን ብቻ እንናገር፣ ራሳችንን በተቻለ መጠን በመግለፅ ስለ ስህተታችንም ይቅርታ እንጠይቅ፡፡
- ነውጠኛነት የአንድን ሰው አለማወቅ የሚገልጥ የሐሰትም ምንጭ ነው፡፡
- ስለዚህ በሐሰት ከሚገኝ ክብር ይልቅ በእውነት የሚገንን መከራ እንምረጥ፡፡
- ሐሰት በተገለጠች ጊዜ በመጨረሻ የሀፍረትን ሸማ ታለብሳለች፡፡
- ሐሰትን ለመሸፈን ከመዋሸት ሐሰቱን ተረድተን ንስሐ እንግባ፡፡
- «ከሐሰት ነገር ራቅ እኔ ኃጢአተኛውን አላጸድቅምና ንጹሕንና ጻድቅን አትግደል።» ***<u>ዘጸ 23፡7፡፡</u>***
- «ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይቀርም በሐሰትም የሚናገር ይጠፋል።» ***<u>ምሳ 19፡9፡፡</u>***
- «ሰዎችም ተነሥተው። እኔ ይህን በእጅ የተሠራውን ቤተ መቅደስ አፈርሰዋለሁ በሦስት ቀንም ሌላውን በእጅ ያልተሠራውን እሠራለሁ ሲል ሰማነው ብለው በሐሰት መሰከሩበት።» ***<u>ማር 14፡57-58፡፡</u>***
- «ጭፍሮችም ደግሞ። እኛ ደግሞ ምን እናድርግ? ብለው ይጠይቁት ነበር። እርሱም፡- በማንም ግፍ አትሥሩ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ፥ ደመወዛችሁም ይብቃችሁ አላቸው።» ***<u>ሉቃ 3፡14፡፡</u>***
- «ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።» ***<u>ካል ተሰ 2፡11-12፡፡</u>***

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

ይቆየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።